# ቀና በል ተው መለሰ

ክስተት ተደርቦ ከሰውልጅ ምግባሩ
ጊዜ ከዘመኑ ተቀናጅቶ ውሉ፤

አጋጣሚ ግኝት እየተዋሃዱ
ስም ለሰው ይሰጣል ሊሆን ምልክቱ ፤

ሲመረመር ሲቃኝ መለሰ ስንክሳሩ
ከአገረ ኢትዮጵያ ራብ ፡ ችነፈር ሊጠፋ ሊከስሙ ፤

መለስ መወደስ ቃሉ
ሊገራው ተነሳ ሰቆቃን ከምድሩ ፤

ቦ ሰላም ለኢትዮጵያ ብልህ የሰበክ
ለባንዴራዋ ክብር በፅናት የቆምክ ፤

ለሃገረ ኢትዮጵያ ቅርያች ተቆርቋሪ
ደንበር የተሻገሩ የማንነታችን አሻራ ሰብሳቢ፤

የመራራቅን ደንቀራ አጥር የናድክ
የወገንን በአንድ መትመም ትብዕል የመለስክ፤

በአክሉነት አብሮ የምኖር ውዳሴን የደገምክ
የአጉል ዕምነት አዚምን የሰበርክ፤

መለሳት ምድረ አቢሲኒያን መለስ እንደስሙ
ወደ ማንነቷ ወደ ጥንቷ ውሉ፤

ትልሙ ገዛፊ ሰናቂ ተስፋ
ለአገር ኩራት ማገር ለአፍሪካ፤

ስሙ ገናና በዓለም መድረክ
የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ የማትበገር፤

እወይ የኛው እድል ማር ሲሉት እሬት
ድሎት ሰፈር ኖሮ ሃዘን በአንድ ሌት ፤

እንዲህ ያለ መሪ የሩቅን አራዕዮ
ማጣት ከእልፍኙ ከላይ ከአትሮኖሱ ፤

እንባ ወረድ ወረድ
ኮብለል በል በደርት ።

የሃገሬ ወጉ ነው ደረት መደሰቁ
ገላነን ቦጫጭቆ ፀጉርነን መንጨቱ ።

ነፍሱነን ሊሰዋ በምትክ መሻቱ
ከማይቻለው ጋር ግብ ግብ መግጠሙ ።

አትፍረዱባቸው ግራ ቢገባቸው
የጀግናዉ መለየት እያስጨነቃቸው ።

ሞትማ  ይሞታል ሁሉም የአዳም ልጅ
የመለስ መለየት እንግዳ ሆነ እንጂ ።

ሀገሬ ኢትዮጵያ በጣሙን አዘነች
በሙሾ እንጉርጉሮ ምድር ቁና ሆነች ።

እንደአባይ ጣና ሸበሌ ገናሌ
በዕንባ ወንዝ ራሱ ምድሯ የሃገሬ ።

ቀና ብልህ እየን ጀሮህን አዘንብል
አንድ አፍታ ተመለስ ለወገንህ ስትል ።

ሩሩህ አንጀትህ ተላላው ልብህ
እስኪ እንደድሮው አንዴ እሺ ይበል ።

የሃገረ ኢትዮጵያን ዕርግዶና ሃዘን
አንዴ ቀኘት አርገና ልብህ ይሰነይ ።

ሃገረ ኢትዮጵያ በሃዘን ራደች
ደፈረሰ ወንዟ ምድርዋም ተረበሸች ።

እንስሳት በሙሉ ወገሹ አላዘኑ
ዕፅዋት ጠውልገው ወደ ጎን ዘመሙ ።

ሲቃ ተናነቀን ቃል ልሳን ሰለለ
ኧረ ተው ተመለስ አይሆንም እያለ ።

ተራራ ቋጥኙ ሜዳ ሸንተረሩ
ድምፀ ቃል አሰሙ ዘይገርም ነገር መለስ መለስ አሉ ።

ማቅ ለበሰ ዙሪያ ገብ ምድሩ
ሰማይ ጉም አዘለ ዡበብ ጥላሸቱ ፤

ማረሻው ለገመ ሞፈሩ ቀንበሩ
አጣምጁ መለሰ ካልመጣ እያሉ ፤

መገረም ድግርግር ከታላቅ ከደቂቅ
ለሆሳስ መደንዘዝ ዕንባ ወረድ ወረድ ፤

የዋህ አዛኝ ነበር ገቢር ባህሪው
የዐዳም ዘር ገረመው እንዲህ መጨከኑ ፤

በክፉ ያንሱህ ምላስ ተሸበበ
እንገታቸው ደፉ ወደምድር ዶለ ፤

የኢትዮጵያ ዕንባ እንደሳት ፈጃቸው
አርምሞ ሊሆን ነው ከአንግዲህ ውሏቸው ፤

አባይ ገመገሙ አጉረመረመ አሉ
ሲያጣ እኩያውን ከቀየው ከጎኑ ፤

የጣድከው ድስት በስሎ ማድ ሊቀርብ ሲል
እንግዶቹ ታድመው ሊቋደሱ አብረውህ ፤

ምነው ዘገየ አሉ ቡራኬህ ይበጃል
መለስ መለስ በሉ ከእልፍኙ ይገኛል ፤

አወይ ወንድም ፤ አባት የመላው ልጅ መለስ
ቁርጥ አረገው መሰል ሄደ ላይመለስ ፤

የበርሃው ፋኖ የጠሩ ገበዝ
አነጣጥሮ ተኳሽ ቃታን ሲመርዝ ፤

ግብግብ ገጣሚ አይፈሬ ቆፍጣና
አተራማሽ ገብቶ ከጠላት ወረዳ ፤

ገንባሌ አስተጣጠቅ ዝናሩ ያማረ
ከወገኑ ጦር ጋር አብሮ የተመመ ፤

ትምህርቱን እንደጌጥ ሲሻው ያጠለቀ
ለወገን ነፃነት ቅድሚያ ያሻል ያለ ፤

መለስ ብሎ ላየ የመለሰን ገቢር
መቸ ለኔ ብሎ ከኢትዮጵያ በቀር ፤

ይህ ሁሉ መወደስ ዜና ቅኔ አቋቋም
የስንኙ ድርደራው የክያኒያን ዜማ ልሳን ፤

ከፕላኔቶቹ ሁላ ላቅ ረቀቅ ብላ
መሬት ተፈጥራለች የአዳም ዘርን አቅፋ ፤

ከአያሉ በታች ገዘፍ ደጎስ ብለው
የሚያስጭንቁ አሉ እንዳሻው ዘውረው ፤

ያንተነን ርትዑ ልሳን ዕውቀት መግዘፍ ሲያዩ
ከየት ምድር መጣ ብለውም ጠየቁ ፤

በጣም ተደመሙ ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ
ዓለምን ዳሰሱ በሚገባ ቋንቋ ትርጁማን ሳይሹ ፤

የዚያች የአያሏ የኢትዮጵያ ፍሬ መሆንክን አወቁ
አንተም ነገርካቸው ኢትዮጵያ አትዮጵያ እያሉ ዘመሩ፤

መዘወር መሪውን ማሽከርከር ቢዳዱ
ኢትዮጵያዊው ሹፌር አንተ ነበርክ አሉ፤

ነጎዱ በረሩ ወደ ኢትዮጵያ አቀኑ
በስራህም ኮሩ ታላቅ እንዳረካት አዩ መሰከሩ፤

ለነሱ እንቆቅልሽ ለኛ ራስ ምታት
ኧረ ሆኖብናል ከመደረክ ዙፋንህ ከመቅፅበት መራቅ፤

አሸራህ አይደርቅም ትውልድ ያነሰዋል
አርማህን አንግቦ ከዳር ያደርሰዋል፤

መለስ እንደሰምህ እስኪ አንዴ ተመለስ
የሕዝበ ዓለምን ውዳሴህን ልበስ ።

## ከተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ/